በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር



የቅድመ-አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት እጩ መምህራን ምልመላና መረጣ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1155/2019

ጥቅምት 2019 ዓ.ም

አዲስ አበባ

መመሪያ ቁጥር 1155/2019

የቅድመ-አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት እጩ መምህራን ምልመላና መረጣ አፈጻጸም መመሪያ

ጥራት ያለው ትምህርት ለዜጎች ተደራሽ ለማድረግ እና የትምህርት ሥርዓቱን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ብቃት፣ ፍላጎት እና ተነሳሽነት ያላቸው መምህራንን ማፍራት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ባለፉት ዓመታት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ እና የማለፊያ ነጥብ ያስመዘገቡ አመልካቾች በመመልመል በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት እንዲሰለጥኑ ቢደረግም የምልመላ ሥርዓቱ የተፈለገውን ብቃትና ዝግጁነት ያላቸውን አመልካቾች ለመምረጥ ውጤታማ ሆኖ ባለመገኘቱ ፤

የትምህርት ጥራትን ከመጠበቅ አኳያ እና ከተደረገው የትምህርት ስርዓት ለውጥ ጋር ተያይዞ የምልመላ ሥርዓቱን መሠረታዊ ለውጥ ማድረግ በማሰፈለጉ ለሙያው ተገቢውን የብቃት ደረጃ ፍላጎትና ተነሳሽነት ካላቸው አመልካቾች መካከል አወዳድሮ በመምረጥ ለየደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸውን ብቁ መምህራን ማፍራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ትምህርት ሚኒስቴር በአጠቃላይ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1368/2017 አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ (3) እና አንቀጽ 94(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት፣ ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**የቅደመ-አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት እጩ መምህራን ምልመላ እና መረጣ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1155/2019**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ ወይም የኃረጉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ “ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

2/ “ትምህርት ቢሮ” ማለት በክልል ወይም ከተማ አስተዳደር የተቋቋመ ትምህርትን በበላይነት የሚመራ የክልል አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በሚወጡ አዋጆች የተቋቋመ የአስተዳደር መዋቅር ነው፤

3/ “እጩ መምህር” ማለት ለመምህርነት ሙያ የሚሰጠውን የቅድመ ስራ ላይ ስልጠና እየተከታተለ ያለ ሰልጣኝ ነው፤

4/ “ትምህርት ጽህፈት ቤት” ማለት በወረዳ ወይም በልዩ ወረዳ ወይም በክፍለ ከተማ ደረጃ የትምህርትን ስራ በበላይነት የሚመራና የእጩ መምህራንን ምዝገባና ምልመላ በበላይነት የሚሰራ የትምህርት ባለድርሻ ተቋም ነው፤

5/ “ትምህርት መምሪያ” ማለት በዞን ደረጃ የትምህርትን ስራ በበላይነት የሚመራ የትምህርት አሰተዳደራዊ አደረጃጀት ነው፤

6/ “ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት” ማለት የህፃናትን ሁለንተናዊ ዕድገት በማጎልበት ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚያዘጋጅ የትምህርት እርከን ነው፤

7/ “አንደኛ ደረጃ ትምህርት” ማለት ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥበትና መሰረታዊ እወቅትና ክህሎት የሚጨበጥበት የትምህርት እርከን ነው፤

8/ “መምህራን ትምህርት ኮሌጅ” ማለት የቅድመ አንደኛ እና የአንደኛ ደረጃ መምህራን የሚያሰለጥን የትምህርት ተቋም ነው፤

9/ “አዎንታዊ ድጋፍ” ማለት ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን ለማበረታታት በህግ የተፈቀደ በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ ድጋፍ ነው፤

10/ በዚህ መመሪያ ውስጥ **በወንድ** ጾታ የተገለጸው ሁሉ **ሴትንም** ያጠቃልላል፡፡

3. <u>ተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የቅደመ-አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት እጩ መምህራን ምልመላ እና መረጣን በሚመለከት በሀገር-አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>ምልመላና መረጣ</u>

4. <u>የምልመላ መስፈርት</u>

ለቅደመ-አንደኛ እና ለአንደኛ ደረጃ መምህርነት ስልጠና ለመወዳደር የሚቀርቡ አመልካቾች የሚከተሉትን የጋራ የምልመላ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡-

1/ ለሰርተፍኬትና ለዲፕሎማ የመምህርነት ሙያ ስልጠና የሚመለመሉ አመልካቾች በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና 50% እና በላይ የስመዘገቡ መሆን አለባቸው፡፡ ይሁን እንጂ በቂ ተወዳዳሪዎች ማግኘት በማይቻልበት ጊዜ ትምህርት ሚኒስቴር በየዓመቱ በሚያወጣው የመቁረጫ ነጥብ መሠረት የሚወዳደሩ ይሆናል፤

2/ አመልካቾች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉት የትምህርት ደረጃዎች ያመጡት አማካይ የትራንስክሪፕት ውጤት 50 ከመቶ እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፤

3/ ውድድሩ የሚካሄድበትን ዓመት እና ከውድድሩ ዓመት ተከታታይ ሁለት አመት ወደኋላ ጨምሮ የመመልመያ መስፈርቱን የሚያሟሉ አመልካቾች መወዳደር ይችላሉ።

5. <u>የትምህርት ማስረጃ</u>

የዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቾች የሚከተሉትን የትምህርት ማስረጃዎች ማቅረብ አለባቸው፡-

1/ ሕጋዊነቱ የተረጋገጠ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት (ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል) ትራንስክሪፕት፤

2/ ክልላዊ የ8ኛ ክፍል ፈተና ውጤት ማስረጃ፤

3/ አገር አቀፍ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ሰርተፊኬት።

6. <u>ዕድሜ</u>

የዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተወዳዳሪዎች ዕድሜ አወሳሰን እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1/ የተወዳዳሪዎች ከፍተኛ የዕድሜ ጣሪያ አግባብ ባለው የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይወሰናል።

2/ የተወዳዳሪዎች ዕድሜ የሚሰላው በልደት ሰርተፊኬት ወይም በ8ኛ ክፍል ፈተና ሰርተፊኬት ላይ በተጠቀሰው የልደት ዘመን መሠረት ይሆናል።

7. <u>ጤና ሁኔታ</u>

1/ አመልካቹ ለሙያው አፈጻጸም የሚያስፈልገውን አካላዊ እና አእምሮአዊ ብቃት የሚያሟላ መሆን አለበት፤

2/ አካል ጉዳተኛ አመልካቾችን በተመለከተ ተገቢው ድጋፍና ምቹ ሁኔታ ተሟልቶላቸው የተመደቡበትን የትምህርት ዓይነት ለማስተማር የሚያስችል የክህሎት ብቃት ያላቸው መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤

3/ የመግባባት ክህሎት በሚጠይቁ የትምህርት ዓይነቶች፣ አመልካቹ የመማር-ማስተማር ሂደቱን በብቃት ለመወጣት የሚያስችል የመግባባት ችሎታ በንግግር ወይም በምልክት ቋንቋ መግለጽ የሚችል መሆን አለበት፤

4/ መስማት የተሳናቸውን ወይም የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን የሚያስተምሩ ዕጩዎች፣ እንደ የትምህርት ዘርፉ ባሕርይ አስፈላጊው የቋንቋ ወይም የቴክኒክ ክህሎት ካላቸው በውድድሩ ወቅት ቅድሚያ ይሰጣል።

8. <u>ሥነ-ምግባር እና ለመምህርነት ሙያ ያለው ፍላጎት</u>

ተወዳዳሪዎች በሚከተሉት የሥነ-ምግባር እና የሙያ ፍላጎት መስፈርቶች መሠረት ይገመገማሉ

1/ መልካም ሥነ ምግባር ያለው እና ለዚህም ከሚኖሩበት አካባቢ ወይም ከተማረበት ትምህርት ቤት የጽሑፍ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤

2/ በመምህርነት ሙያ ለማገልገል ሙሉ ፍላጎት ያለው፤

3/ የሚያስተምርበትን አካባቢ የማስተማሪያ ወይም የአፍ-መፍቻ ቋንቋ የሚያውቅ፤

4/ በሚመደብበት የሥራ ቦታ ለማስተማር ፈቃደኛ የሆነ፤

5/ የተመደቡበትን አካባቢ ማኅበረሰብ ወግና ባህል የሚያከብር እና ከማኅበረሰቡ ጋር ተግባብቶ ለመሥራት ፍላጎትና ፈቃደኝነት ያለው፤

6/ በትምህርት ቤት ክበባት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የነበረው እና ለዚህም የጽሑፍ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል።

9. <u>የአመልካቾች ምዝገባ</u>

በምዝገባ ሂደቱ አመልካቾች ያቀረቧቸውን ማስረጃዎች ትክክለኛና የተሟላ ስለመሆናቸው በመዝጋቢው አካል መረጋገጥ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ ምዝገባ የሚካሄደው ከላይ በአንቀጽ 4 እሰከ 8 የተመለከቱ መስፈርቶችን አሟልተው ሲገኙ ብቻ የሆናል፤

2/ ለቅድመ አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ እጩ መምህርነት ተወዳዳሪዎች በየአካባቢያቸው በተዘጋጀው የምዝገባ ቦታ በአካል ወይም በህጋዊ ወኪላቸው አማካይኝነት ቀርበው መመዝገብ ይችላሉ፤

3/ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህርነት የሚወዳደሩ አመልካቾች የትምህርት መስክ ምርጫ ፍላጎትና ብቃት መሰረት ያደረገ ይሆናል።

10. <u>በምልመላ ወቅት ታሳቢ የሚደረጉ ጉዳዮች</u>

1/ ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህርነት ሴት አመልካቾች ብቻ እንዲመለመሉ ይደረጋል፤

2/ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሴት ተወዳዳሪዎች ካልቀረቡ ፍላጎት ያላቸውና የምልመላ መስፈርቱን የሚያሟሉ ወንዶች ይመለመላሉ፤

3/ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህርነት ሴት ተወዳዳሪዎች 30% የውድድ ድርሻ ተይዞላቸው ተወዳዳሪ ይሆናሉ፤

4/ አዎንታዊ ድጋፍ የሚሰጣቸው ተወዳዳሪዎች ከሌሎች ጋር ተወዳድረው እኩል ነጥብ ካመጡ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ይመረጣሉ፤

5/ አዎንታዊ ድጋፍ የሚሰጣቸው ወንድ አካል ጉዳተኛ እና ሴት አካል ጉዳተኛ ተወዳዳሪዎች እኩል ነጥብ ካመጡ ለሴት አካል ጉዳተኛ ቅድሚያ ይሰጣታል፤

6/ ለታዳጊ እና አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚገኙ ተወዳዳሪዎች የክልሉ መንግስት በህግ ለይቶ ባወጣው የአውንታዊ ድጋፍ ህግ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፤

7/ ነፍሰ-ጡር ሴት ተወዳዳሪዎች አስፈላጊውን የምልመላ መስፈርት ካሟሉ ለእጩ መምህርነት መወዳደር ይችላሉ።።

11. <u>ምልመላ</u>

1/ የተመዘገቡ አመልካቾች ምልመላ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማካይ የትራንስክሪፕት እና የአገር አቀፍ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የፈተና ውጤት መሰረት ይሆናል።።

2/ የአመልካቾች ምልመላ ከ100 የሚያዝ ሆኖ፡-

ሀ) ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማካይ የትራንስክሪፕት ውጤት 50%

ለ) የአገር አቀፍ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የፈተና ውጤት 50% ይሆናል።።

3/ የአመልካቾች ምልመላ ከተጠናቀቀ በኋላ ምልመለውን ያለፉ ተወዳደሪዎች ስም ዝርዝር እና ተያያዥ ማስረጃዎች ተደራጅተው ለመግቢያ ፈተና ለመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ይላካል።።

12. <u>መረጣ</u>

1/ የመግቢያ ፈተና በክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ አስተባባሪነት በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፤

2/ የመግቢያ ፈተናው በጽሑፍ፣ በቃለ መጠይቅ እና በእጅ ጽሁፍ ክህሎት ግምገማ ላይ የሚወሰን ይሆናል፤

3/ ተወዳዳሪዎች የጽሑፍ ፈተናና የእጅ ጽሑፍ ክህሎት ፈተና በአንድ ጊዜ ተፈትነው እንዲወጡ ይደረጋል፤

4/ ተወዳዳሪዎች ወደ መምህርነት ስልጠና የሚገቡት የመግቢያ ፈተና ወጤት መሰረት በማድረግ ነው፤

5/ ተወዳዳሪዎች ለቃለ-መጠየቅ ለመቅረብ በጽሑፍ የተሰጠውን ፈተና 50% እና በላይ ማስመዝገብ ይጠበቅባቸዋል።።

13. <u>የጽሑፍ ፈተና ሲዘጋጅ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች</u>

1/ ለአፍ መፍቻና ለእንግሊዘኛ ቋንቋዎች የሚዘጋጁ ጥያቄዎች የተወዳዳሪዎችን አንብቦ የመረዳት፣ የጽሁፍ፣ መረጃን የማደራጀትና የመተንተን ክህሎቶችን መለካት ይኖርባቸዋል፤

2/ የሒሳብ ጥያቄዎች የተወዳዳሪዎችን መሰረታዊ የሒሳብ ስሌት ትምህርት ክህሎት እና እውቀት በነባራዊው አለም ለሚገጥሙት ችግሮች መፍትሄ የመፈለግ ችሎታን ለመፈተሽ የሚያስችሉ ይዘቶች ማካተት አለባቸው፤

3/ የዜግነትና ግብረ ገብ ጥያቄዎች አጠቃላይ ጉዳዮችን የሚፈትሹ ሆነው የሀገር ፍቅር፣ ስነ ምግባር፣ ብዝሃነት እና የስራ ባህል ጽንሰ ሀሳቦችን እንዲያካትቱ ይደረጋል፤

4/ ለአፕቲትዩድ የሚዘጋጁ ጥያቄዎች ተወዳዳሪዎች የተጻፉ መረጃዎችን አንብቦ የመረዳት፤ የመተንተን እና ተስማሚ መፍትሄዎችን የመለየት፤የችግር ፈችነት ችሎታ፣የውሳኔ አሰጣጥ ብቃት የሚለኩ መሆን አለባቸው፤

5/ ለመሰረታዊ የዲጅታል ቴክኖሎጅ እውቀት የሚዘጋጁ ጥያቄዎች መሰረታዊ የኮምፒተርና የአሰራር ስርዓት እውቀት፣የኢንተርኔት አጠቃቀም እውቀት እና የዲጅታል ደህንነትና ስነምግባር ያካተቱ ሊሆኑ ይገባል።

14. <u>የጽሑፍ ፈተና ነጥብ አያያዝና የጥያቄዎች ስብጥር</u>

1/ የጹሑፍ ፈተና ከአጠቃላይ ነጥብ ውስጥ 70% ይይዛል።

2/ የእፌቴ ተወዳዳሪ መምህራን የጽሁፍ ፈተና ጥያቄዎች ስብጥርና የተሰጣቸው ነጥብ በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡-

ተ.ቁ	የጽሑፍ ፈተና የሚያካትታቸው የትምህርት አይነቶች	የጥያቄ ብዛት
1	ሒሳብ	15
2	አፍ መፍቻ ቋንቋ	10
3	እንግሊዘኛ	15
4	ዜግነትና ግብረ ገብ	15
5	አፕቲትዩድ	10
6	መሰረታዊ የዲጅታል ቴክኖሎጂ እውቀት	5
ድምር		70

3/ 15% የእጅ ጽሑፍ ክህሎት መለኪያ ፈተና በጽሑፍ መርህ መሰረት የሚዘጋጅ ይሆናል።

4/ 15% ቃለ-መጠይቁ የዕፌቴ ተወዳዳሪዎችን ለመምህርነት ሙያ ያላቸው እሳቤ፣ የንግግር እና ሀሳብን የመረዳት ክህሎት፤ስነ ምግባርን፣ በራስ የመተማመን፣ ልዩ ድጋፍ የሚሹ

አካላትን ለመርዳት ያላቸው ግንዛቤ በሚለካ መልኩ መዘጋጀት አለበት፤ቃለ-መጠይቁ የሚከናወነው በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ በሚሰለጥኑበት ቋንቋ ሆኖ ነጥብ አያያዙ ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡-

ሀ) ሀሳብን የመረዳት (4%)፣

ለ) የንግግር ክህሎት (4%)፣

ሐ) በራስ መተማመን (3%)፣

መ) ባህሪይ እና አውድ ፈጥኖ የመረዳት (4%) የሚያዝ ይሆናል፡፡

ክፍል ሦስት

የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

15. የትምህርት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

1/ በመመሪያው መሰረት ምልመላና መረጣ መከናወኑን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

2/ እንዳስፈላጊነቱ በአመቱ የእጩ መምህራን ወደ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች የመግቢያ መቁረጫ ነጥብ ሊወስን ይችላል፤

3/ ለእጩ መምህራን መምረጫ ምዘና ማዕቀፍ ያዘጋጃል

4/ የእጩ መምህራን መመልመያና መምረጫ መመሪያ ላይ ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ ይሰጣል፡፡

16. የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

1/ በትምህርት ዓመቱ የእጩ መምህራን ስልጠና ፍላጎት በትምህርት ዓይነት እና በትምህርትእርከን በማደረጃት ለመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ያሳውቃል፤

2/ የመግቢያ የፈተና ዝግጅት በምዘና ማዕቀፍ መሠረት መዘገጋጀቱን ያረጋግጣል፤

3/ የእጩ መምህራን ምልመላና መረጣ ሂደት አስተደዳደራዊ ጉዳዮችን ይመራል፤

4/ ከተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ያጣራል ውሳኔ ይሰጣል፡፡

17. የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተግባርና ኃላፊነት

1/ በተዘጋጀው የምዘና ማዕቀፍ መሰረት የመግቢያ ፈተና ያዘጋጃል፤ፈተና ይሰጣል፤ ውጤት ያሳውቀል፤

2/ በምልመላ ሂደት የተደራጁ የተወዳዳሪዎች ፋይልን ከወረዳ ወይም ከልዩ ወረዳ ትክክለኝነት አረጋግጦ ይረከባል፤በፈተና በትምህርት ማስረጃዎች መሰረት ያለፉ ዕጩ ተወዳደሪዎች ዝርዝር ለሚመለከተው ሁሉ ያሳውቃል፤

3/ በክልሉ በተገለጸው የመምህራን ፍላጎት መሰረት ተወዳድረው ያለፉ እጩ ሰልጣኞችን በየትምህርት መስኩ ይደለድላል፤

4/ በግላቸው በተለያዩ የስልጠና መርሃ-ግብሮች ስልጠና የሚፈልጉ አመልካቾች በዚህ መመሪያ በተመላከቱ የምልመላና መረጣ መስፈርቶች መሟላታቸውን እና ክልሉን የመምህራን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን አረጋግጦ ይቀበላል፡፡

18. <u>የወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1/ የምልመላ የጊዜ ሰሌዳን መሰረት ማስታወቂያ ያወጣል፤

2/ መስፈርቱን አሟልተው የተመዘገቡ አመልካቾችን መረጃ ትክክለኛነት በማረጋገጥ ለመግቢያ ፈተና ብቁ የሆኑትን በመለየት ዝርዝራቸውን ለመምራን ትምህርት ኮሌጅ ይልካል፤

3/ በምልመላ ሂደት ከተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ያጣራል ውሳኔ ይሰጣል፡፡

19. <u>የምልመላ ኮሚቴ</u>

1/ የምልመላ ኮሚቴ እንደክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ከ3 እስከ 5 አባላት የሚኖሩት ሲሆን የኮሚቴው አባላት የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) የወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤት መምህራን ልማት ኃላፊ ... ሰብሳቢ

ለ) የወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤት መምህራን ልማት ባለሙያ.....አባል

ሐ) የወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤት ስርዓተ-ትምህርትና ትግብራ ባለሙያ--አባል

መ) ከወረዳው ትምህርት ጽሕፈት ቤት የሥርዓተ-ፆታ ኃላፊ ... አባል

ሠ) የወረዳው የሰው ሀብት አስተዳደር ባለሙያ..... ጸሐፊ

2/ የኮሚቴው ተጠሪነት ለወረዳ ወይም ለልዩ ለወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት ሆኖ እንደየክልሉ አስተዳደራዊ አደረጃጀት ይወሰናል፡፡

20. <u>የምልመላና መረጣ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1/ የምልመላ መስፈርቶች መሠረት የምዝገባ እና ምልመላ ያከናውናል፤

2/ የአመልካቾችን የትምህርት ማስረጃዎች፣ የትራንስክሪፕት ውጤት፣ የዕድሜ፣ የጤና እና የሥነ-ምግባር ማስረጃዎች ሕጋዊነትና ትክክለኛነት መርምሮ ያረጋግጣል፤

3/ አመልካቾች በትራንስክሪፕት እና በሌሎች መስፈርቶች ያገኙትን ውጤት ያደረጃል፤ ተወዳዳሪዎችን በደረጃ ይለያል፤ በቃለ-ጉባኤ አስደግፎ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

21. **የመተባበር ግዴታ**

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ትብብር የተጠየቀ አካል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

22. **ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ጉዳዮች**

በዚህ መመሪያ ላይ በተሸፈኑ ጉዳዮች ከመመሪያው ጋር የሚቃረኑ መመሪያዎች ልማዳዊ አሰራሮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

23. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ሚኒስቴሩ እንደ አስፈላጊነቱ መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

24. **መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በትምህርት ሚኒስቴር ድህረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ጥቅምት፣ 2019 ዓ.ም

ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ (ፒኤችዲ)

የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር

ሚኒስትር